Energy & Water
Ombudsman NSW
Free, fair and independent

# ከኤሌትሪክ፣ ጋዝ ወይም የውሃ ኣቅራቢ ድርጅትዎ ጋር ያጋጠምዎት ችግር ኣለ?

**EWON** በኒው ሳውዝ ዌልስ ነዋሪ ለሆኑና ከኤሌትሪክ ኣቅራቢ ድርጅታቸው ጋር ችግር ላለባቸው ሰዎች እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ የውሃ ደንበኞችን እናግዛለን።

እኛ **ነፃ**

እኛ **የማያዳላ**

እኛ **ገለልተኛ**

## ያለብዎት ችግር :

- የኤሌትሪክ ወይም የውሃ ሂሳብዎ እንዴት እንደተሰላ ኣልገባዎትም?
- ሂሳብዎን መክፈል ኣልቻሉም?
- እዳ ኣለብዎት ፣ የመክፈል ኣቅም ኣጥሮብዎታል?
- ኣገልግሎትዎ እንዳይቋረጥብዎት ሰግተዋል?
- በኣቅራቢው ድርጅት የደንበኛ ኣገልግሎት ደስተኛ ኣይደሉም?
- ኣዲስ ደንበኛ ለመሆን ወይም የቆዩበትን ደንበኝነት ለማቋረጥ ተቸግረዋል?
- የተሻለ ኣገልግሎት በተሻለ ዋጋ ለማግኘት ይፈልጋሉ?

## እንዴት እንርዳዎ?

- ችግርዎን እናዳምጣለን፤ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለመወሰን እንረዳዎታለን።
- ኣስተርጓሚ ካስፈለግዎት እንጠራልዎታለን።
- የኣቅራቢው ድርጅት ከፍተኛ ባለ ስልጣን ደውሎ እንዲያነጋግርዎት እናመቻቻለን።
- የተሻለ ውጤት ማግኘት የሚችሉበትን ድርድር እንዲያካሂዱ እንረዳዎታለን።
- ቅሬታዎን እንመረምርልዎታለን።
- መርዳት ካልቻልን ወደ ሌላ ድርጅት እናስተላልፍዎታለን።

## በሂሳብ ኣከፋፈል ላይ እንድንረዳዎ ይፈልጋሉ?

- ሂሳብዎን በወቅቱ መክፈል ካልቻሉና እዳዎ እየበዛ እንዳይሄድ በቅድሚያ ኣቅራቢውን ድርጅት ያነጋግሩ።
- የእዳ መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምልዎ እናደርጋለን።
- የእዳ መክፈያ እቅድ በማውጣት እዳዎን ቀስ በቀስ የሚከፍሉበት መንገድ ለማመቻቸት መደራደር እንዲችሉ እንረዳዎታለን።
- ኣቅምዎ በሚፈቅደው መንገድ መክፈል የሚችሉበት መርሃ ግብር ላይ እንዲሳተፉ እንረዳዎታለን።
- ሂሳብዎን ለመክፈል ገንዘብ የሚቆጥቡበት መንገድ እናሳይዎታለን።
- የገንዘብ ኣያያዝና ኣጠቃቀም ማግኘት በሚችሉበትን መንገድ ላይ መረጃ እንሰጥዎታለን።

## ቅሬታዎች የሚፈቱባቸው መንገዶች

- ከኣገልግሎት ኣቅራቢው ድርጅት ጋር ችግር ካለብዎት ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ ያስረዷቸው።
- ጓደኛ ወይም ሌላ የቤተሰብ ኣባል ችግርዎትን ኣብራርቶ እንዲያስረዳልዎት ይጠይቁ።
- ኣስተርጓሚ ከፈለጉም ድርጅቱን ይጠይቁ።
- የተላኩልዎት ደብዳቤዎች፣ ያነጋገሩዋቸው ሰዎች ስምና ያነጋገሩበት ቀንና ሰዓት በሚገባ ይመዝግቡ።
- ጥሪ ተቀባይ ሰራተኞች ችግርዎን መፍታት ካልቻሉ፤ የበላይ ባለ ስልጣን እንዲያነጋግርዎት ይጠይቁ።
- ይሄንን ሁሉ ኣድርገው ችግሩ ካልተፈታ እኛን ያነጋግሩ።

## እኛን እንዴት ሊያነጋግሩን ይችላሉ?

**ኣስተርጓሚ በመጠቀም እኛን ሊያነጋግሩ ይችላሉ**

የትርጉም ኣገልግሎት የስልክ ቁጥር **131 450** ላይ በቀጥታ በመደወል እኛን ማነጋገር እንደሚፈልጉ ይጠይቁ።

ጓደኛ፣ የቤተሰብ ኣባል ወይም የማህበረሰብ ሰራተኛ እኛን እንዲያነጋግርልዎም መጠየቅ ይችላሉ።

**በስልክ ቁጥር 1800 246 545 በነፃ ይደውሉልን**

(ከሞባይል የሚደውሉ ከሆነ ይንገሩንና እኛ ራሳችን መልሰን እንደውልልዎታለን።)

በቀጥታ ድረ መስመር ላይ ቅሬታዎን ለመግለፅ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ

**www.ewon.com.au ድረ ገፃችንን ይጎብኙ።**